በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፕላንና ልማት ሚኒስቴር

# የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ጥር 2014፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ማውጫ

ድርሞ ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- 1

መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- 3

ክፍል 1፡- የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ------------- 4

ሠንጠረዥ 1፡- የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዋና ዋና ተግባራት መለኪያ፣ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀም ---------------------------------------------------------------------------------------------- 4

የ100 ቀን ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ------------------------------------------------------------------------29

ለተጠሪ ተቋማት የተደረገ ክትትልና ድጋፍ -----------------------------------------------------------------29

የውጪ ኦዲት ስራዎችን በተመለከተ -----------------------------------------------------------------------29

ገበታ ለሀገር ሀገራዊ ፕሮጀክት በተመለከተ-------------------------------------------------------------------29

የሪፎርም ስራዎችን በተመለከተ ---------------------------------------------------------------------------29

በአፈፃፀም ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች -----------------------------------------------30

ሠንጠረዥ 2. የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት (የመደበኛው በጀት) የበጀት አጠቃቀም --------------------------------------------------------------------------------------------31

ሠንጠረዥ 3. የፕላንና ልማት ሚኒስቴር እና የተጠሪ ተቋማት የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የበጀት አጠቃቀም --------------------------------------------------------------------------------------------32

ክፍል 2፡- የተጠሪ ተቋማት የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዋና ዋና ግቦች የዕቅድ አፈፃፀም -----33

ሠንጠረዥ 4፡- የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዋና ዋና ግቦች የዕቅድ አፈፃፀም-------------------------------------------------------------------------------------34

ሠንጠረዥ 5፡-የፖሊሲ ጥናት ኢኒስቲትዩት የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዋና ዋና ግቦች የዕቅድ አፈፃፀም ------------------------------------------------------------------------------------------46

ሠንጠረዥ 6፡- የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዋና ዋና ግቦች የዕቅድ አፈፃፀም ------------------------------------------------------------------------------------------50

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፕላንና ልማት ሚኒስቴር

## ድርሞ

ለ30 ዓመት የልማት ዕቅድ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች እንዲሁም የጥናት ውጤቶች እየተሰባሰቡ ይገኛሉ። የስፓሻል ፕላን ማዕቀፍ ይዘቶች እንዲሁም የድርጊት መርሃግብር ተዘጋጅቷል። የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ ለማዘጋጀት የልማት ዕቅድ ፅንሰ ሃሳብ ተዘጋጅቷል። የ2014 በጀት ዓመት ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቷል። የ2014 በጀት ዓመት እና የ3 ዓመት (2014-2016 በጀት ዓመት) የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል።

ብሔራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ የዋጋ ግሽበት በኢኮኖሚዉ ላይ እያደረሰ ያለዉን ጫና ለመቆጣጠር የሚያስችል ፕሮግራም ነድፎ ተግባራዊ ለማድረግ ባስቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ለዋጋ ንረት ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች ላይ ትንታኔ የሚያደርጉና የመፍትሄ ሃሳቦችን የሚያስቀምጡ ጥናቶችን እንዲያካሄዱ ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ የሚኒስቴር መ/ቤቶች አቅጣጫ ሰጥቷል። በመሆኑም የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ስራውን የማስተባበር ሃላፊነቱን በመውሰድ የተለያዩ ቴክኒካል ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

የአስር ዓመቱ (2013-2022) የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የተቀናጀና ወጥ የሆነ የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት ከዘርፍ አስፈጻሚ መ/ቤቶች የአፈፃፀም መረጃዎች በማሰባሰብ የዘርፍ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቷል። 383 የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ 24 የግድብና መስኖ ፕሮጀክቶች፣ 21 የኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማከፋፊያ ፕሮጀክቶች፣ 14 የኢንዱስትሪያል ፓርክ ፕሮጀክቶች፣ 6 የስኳር ፕሮጀክቶች፣ 3 የባቡር ፕሮጀክቶች እና 11 የፌዴራል የመንግስት ቢሮ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቷል። በሦስት ዘርፎች ማለትም በግድብና መስኖ፣ በኢነርጂ እና በመንገድ ዘርፍ አራት ፕሮጀክቶች ማለትም በካሊድ ዲጆ ግድብና መስኖ፣ አዳማ 2-230/132/15 ኪሎ ቮልት የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ፣ መልካሳ-ሶደሬ-ኑራሄራ-መተሀራ መንገድ እና የኢተያ-ሮቤ አገናኝ መንገድ ፕሮጀክቶች የመስክ ምልከታ ተካሄዷል።

የ2014 በጀት ዓመት የ1ኛ ሩብ ዓመት የተጠቃለለ የመሰረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ሪፖርት ከማዘጋጀት አንፃር የመንገድ፣ የግድብና መስኖ፣ የኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማከፋፊያ፣ የኢንዱስትሪያል ፓርክ፣ የስኳር ልማት፣ የባቡር መስመር ዝርጋታ፣ እና የፌዴራል የመንግስት ቢሮ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም የፕሮጀክቶች የፊዚካልና ከፋይናንስ አፈፃፀም፣ ፕሮጀክቶች በመዘግየታቸው ምክንያት ከአስከተሉት ወጪ፣ በበጀት ዓመቱ ከአጋጠሙ ችግሮችና ከተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ አንፃር ትንተና ተካሂዶ አንድ ትንተና ሰነድ ተዘጋጅቷል።

የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ከቅድመ-ትግበራ ስርዓት፣ ከፕሮጀክቶች ክትትል ስርዓት (ከዴስክ ሪቪውና ከመስክ ክትትል አንፃር፣ ከፕሮጀክቶች ግምገማ ስርዓት (ከቅድመ-ትግበራ፣ ከአጋማሽ ዘመን ግምገማ፣ ከመጨረሻ ዘመን ግምገማ እና ከፕሮጀክቶች ስኬትና ፋይዳ ግምገማ)፣ ተሞክሮዎችን ከመቀመርና ተደራሽ ከማድረግ እንዲሁም ከአስቻይ ሁኔታዎች ማለትም ከቅንጅታዊ አሰራር፣ ከአቅም ግንባታ እና ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አንፃር በመከታተልና በመገምገም አፈፃፀማቸውን ማሻሻል የሚያስችል የፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ የአሰራር ስርዓት ሠነድ ተዘጋጀቶና በየደረጃው ግብዓት ተሰጥቶበት የመጨረሻ ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጎ ቀርቧል።

ለ76ኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ግብዓት የሚሆን የተጠቃለለ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈጻጸም ተዘጋጅቶ ቀርቧል። የአፍሪካ የልማት አጀንዳ (አጀንዳ 2063) የመጀመሪያው 10 ዓመት ትግበራ ሁለተኛው ዙር የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ቀርቧል። ከተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት አድን ድርጅት ጋር በመሆን ሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም ዝግጁነት የዳሰሳ ጥናት በመካሄድ ላይ ሲሆን ረቂቅ ጥናቱ ተዘጋጅቷል። በቀጣይ በጥናቱ መሠረት የአቅም ግንባታ መርሃ-ግበር ይዘጋጃል። የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን በዲጂታል ሪፖርት ማቅረቢያ ሥርዓቱ በኩል ማቅረብ ከመጠበቅባቸው 26 ተቋማት ውስጥ 11 ተቋማት አቅርበዋል። ከነዚህም ውስጥ 7 ተቋማት በቀረበው መመዘኛ መስፈርት መሠረት የልማት ዕቅድ ትግበራቸውን በመመዘን ለማመላከት ሞክረዋል። የፌዴራል ተቋማትን የፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ አሰራር፣ አደረጃጀትና የሰው ኃይል በዳሰሳ ጥናት ለመለየትና ድጋፍ ለማድረግ ርዕስ የመለየት፣ የ2ኛ ደረጃ መረጃ የመሰብሰብ እና የአንደኛ ደረጃ መረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ የማዘጋጀት ሥራ ተከናውኗል።

የዘርፈ ብዙ የድህነት አመልካች (MPI) ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል የመነሻ የጥናት ሰነድ በመዘጋጀት ላይ ነው። የዘርፈ ብዙ ድህነትን ለመለካትና ለመተንተን የቤተሰብ ገቢና ወጪ የናሙና ጥናት (HCES)

እና የኑሮ ደህንነት የናሙና ጥናት (WMS) መረጃዎች በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ። ኢ-እኩልነት በረዥም ጊዜ ሁኔታ ለድህነት መባባስ ምክንያት ሊሆን የሚችልባቸውንና የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖ ጥናት ለማጥናት የጥናቱ መነሻ ሀሳብ ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም ከ/WRI/ ጋር በመተባበር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። የብሔራዊ የሰው ሀብት ልማትና የስራ ገበያ ግምገማዊ ጥናት (National human capital development and labour market evaluation study) መነሻ ፅንስ ሃሳብ ተዘጋጅቷል።

በፅንስ ሀሳብ ደረጃ እንዲሁም አዋጭነት ግምገማ ተዘጋጅቶላቸው ለቀረቡ የልማት ፕሮጀክቶች ግምገማ በማድረግ ውሳኔ እና ምላሽ ተሰጥቷል። የፕሮጀክት ፅነሰ ሀሳብ፣ የአዋጭነት ጥናት እና የትግበራ ዕቅድ መመሪያዎች ያለባቸውን ክፍተት ለመሙላት መመሪያዎቹ እንዲሻሻሉ ተደርጓል። ከግብርና እና መስኖ፣ ከከተማ ልማት፣ ከከፍተኛ ትምህርት ሴክተሮች እና ከተለያዩ የፌደራል መ/ቤቶች የቀረቡ የፕሮጀክቶች አዋጭነት ጥናት ላይ የአዋጭነት ግምገማ በማከናወን ለምላሽ ዝግጁ ሆነዋል። የሴክተሮችን የኢንቨስትመንት የትኩረት አቅጣጫ የሚያሳይ የኢንቨስተመንት ፕሮግራም በማዘጋጀት ለሴክተሮች ተደራሽ በማድረግ በልማት ፕሮግራም እንዲያዝ ተደርጓል። የከፍተኛ ትምህርት የመንግስት ኢንቨስትመንት አስተዳደር የሚመራ አመላካች ረቂቅ ስትራቴጂ ተቀርፃል።

የ2013 በጀት አመት በጊዜውና በቋሚ አመት ዋጋ የተሰላ አመታዊ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት Supply Side GDP እና ከአጠቃቀም አንፃር (Expenditure Side GDP) ግመታ ተዘጋጅቶ ቀርቧል። የ2013 4ኛው ሩብ ዓመት የሀገራዊ ምርት ግመታ (QGDP - Supply side) ከአቅርቦት አንጻር ተዘጋጅቷል። የኢትዮጵያ የክልል ኢኮኖሚ አካንት መመሪያ (Sources and methods manual) ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

ለሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ክለሳ ግብአት የሚሆኑ የሥነ ሕዝብና ልማት ፖሊሲ መግለጫ ጥናቶች (Pathways to Accelerate the Process of Demographic Dividend in Ethiopia ፣ Redressing Regional Disparities in Fertility Levels in Ethiopia: Priority Intervention Areas, እና Raising Age at First Marriage as a Factor Contributing to the Reduction of Fertility in Ethiopia) በዘርፉ ልምድ ባላቸው አማካሪዎች ተካሂደው ተጠናቀዋል። በተጨማሪም በሥራ አጥነት ችግሮች (Unemployment Problems) ፣ በወጣቶች ፍልሰት (Youth Migration) እና በስነ ህዝብ ትርፍ ድርሻ (Demographic Dividened) ላይ ጥናቶች ተካሂደው የጥናቶቹ የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነዶች ተዘጋጅተው ቀርቧል።

# መግቢያ

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ተልዕኮ ለአገሪቱ ዘርፈ ብዙ የልማት መስኮች የፖሊሲ ትንታኔዎችን፣ አመራር እና ድጋፍ መስጠት፣ የሴክተር መስሪያ ቤቶችን እና የመንግሥት ተቋማትን በማቀናጀት የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶችን ማዘጋጀት፣ ለልማት ፖሊሲ፣ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች መረጣ፣ ግምገማ እንዲሁም ቅደም ተከተል እንዲረዳ የመንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደር እና አመራር አቅም ማጎልበቻዎችን ማበልፀግ፣ በልማት ዕቅዶች፣ ፖሊሲ እና ፕሮግራሞች ላይ ወቅቱን ጠብቆ ቁጥጥር እና ግምገማ ማካሄድ እንዲሁም ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት እና ሌሎች የማክሮ ኢኮኖሚ ግመታዎችን ከሴክተሮች ትንታኔ ጋር ያጠቃለለ መደበኛ አካውንት ማዘጋጀት ነው። አላማውም ሁሉም አገራዊ የልማት ዕቅዶች በአግባቡ የታለመላቸውን ግብ መምታቸውን ማረጋገጥ ነው።

ከዚህ አኳያ መ/ቤቱ በ2014 በጀት ዓመት በርካታ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ተግባራት ለማከናወን አቅዷል። ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የ30 ዓመት ዕቅድ ማዘጋጀት፣ የድህነትና የኑሮ ደህንነት ትንተና ስራ ማካሄድ፣ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ሞዴሎችን መቅረፅ፣ የልማት ዕቅዱን አፈፃፀም መከታተልና መገምገም፣ የዲጂታል ክትትልና ግምገማ ስርዓቱን ማጠናከር፣ የልማት ፕሮጀክቶች አዋጭነት ግምገማ፣ ብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንቶችን ማዘጋጀት እና የስነ-ህዝብ ፖሊሲ ክለሳ ማካሄድ ናቸው።

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተጣለበት ተግባርና ኃላፊነት የተመነዘረ አመታዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ይገኛል። በዚህም የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትና የአፈጻጸም ደረጃ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች እንዲሁም የተጠሪ ተቋማት (የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት፣ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲዩት እና የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን) የዋና ዋና ግቦች የዕቅድ አፈጻጸም አካቶ ተዘጋጅቷል።

# ክፍል 1፡- የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም

## ሠንጠረዥ 1፡- የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዋና ዋና ተግባራት መለኪያ፣ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀም

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| | | **የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች፤ (ክብደት 13)** | | | | | |
| 1 | **የእቅድ ዝግጅት** | | | | | | |
| 1.1 | የሚኒስቴር መ/ቤቱን የ2014 በጀት አመት ዕቅድ ማዘጋጀት | • የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተልኳል፡፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 1.2 | የሚኒስቴር መ/ቤቱን የ2014-2017 በጀት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት | | በቁጥር | 1 | 0 | 0 | ከመ/ቤቱ አዲስ አደረጃጀት እንዲሁም ከተሰጡት ተጨማሪ ተግባርና ሃላፊነቶች የተመነዘረ ከ2014-2017 በጀት ዓመት የሚቆይ ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በስራ መደራረብ ምክንያት አልተከናወነም፡፡ በቀጣይ የ3 አመት (ከ2015-2017) ዕቅድ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ |
| 2 | **የፈጻሚ ዝግጅት** | | | | | | |
| 2.1 | የኮሚሽኑን የሰው ሃብት በበጀት አመቱ መጨረሻ 250 ማድረስ | • በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ውስጥ 12 ሰራተኞች (1 ወንድ ሰራተኛ በቋሚ ቅጥር፣ 11 ሰራተኞች (6 ወንድ፣ 5 ሴት) ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም ከፀረ-ሙስና ኮሚሽን በምደባ) መ/ቤቱን ተቀላቅለዋል፡፡<br>• በዚህም 26 ሰራተኞችን ለማሟላት ታቅዶ 12 ሰራተኞች ብቻ ተሟልተዋል፡፡<br>• በተጨማሪ 13 ሰራተኞች በኮንትራት ቅጥር እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡<br>• 10 ሰራተኞች (8 ወንድ 2 ሴት) መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡ | በቁጥር | 26 | 12 | 46.15 | የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቋሚ ቅጥርን በመከልከሉ ምክንያት አስፈላጊ የሆኑት የስራ መደቦች በኮንትራት ቅጥር ተሟልተዋል፡፡ |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.2 | ዘመናዊ የሰው ሀብት መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ሲስተም (ICSMIS) ተግባራዊ ማድረግ | • በአዲሱ የመ/ቤቱ አደረጃጀት መሰረት ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባለሙያዎች ጋር በመሆን የሰራተኞች መረጃ በአዲስ መልክ ወደ ሲስተሙ ገብቷል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 80 | 80 | ለባለሙያዎች የICSMIS ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ስለሆነ ሲስተሙን መሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም፡፡ በቀጣይ ስልጠናው ተሰቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ |
| 2.3 | የአመራር እና የባለሙያ አቅም በረጅም፣በመካከለኛ እና በአጭር ጊዜ ትምህርትና ስልጠና መገንባት | | | | | | |
| 2.3.1 | ለመ/ቤቱ ባለሙያዎች (የውጭ ሀገር እና የሀገር ውስጥ) የ2ኛ ዲግሪ (MA, MSc) እና የ3ኛ ዲግሪ (PhD) የትምህርት ዕድል ማመቻቸት | • 4 የመ/ቤቱ ሰራተኞች (2 ሴት፣ 2 ወንድ) የሀገር ውስጥ የ2ኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል አግኝተዋል፡፡ ከ4ቱ ሰራተኞች 1 ሰራተኛ ትምህርታቸውን አቋርጠዋል፡፡<br>• የጃፓን መንግስት ለመ/ቤታችን በሰጠው የረዥም ጊዜ የትምህርት ዕድል በማስተርስ ዲግሪ ሰራተኞችን በማወዳደር 1 ወንድ ሰራተኛ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የውድድር ሂደቱ ተጠናቆ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡ | በቁጥር | 4 | 4 | 100 | |
| 2.3.2 | ከሥራ ክፍሎች የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት | • የስራ ክፍሎች የስልጠና ፍላጎታቸውን እንዲልኩ መረጃ ተልኳል፡፡<br>• ለ28 ሰራተኞች በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በ11 የስልጠና ርዕሶች ላይ ስልጠና እንዲወስዱ ማድረግ ተችሏል፡፡<br>• ለ10 ሾፌሮች "በአውቶ መካኒክነት" እና ለ4 ሾፌሮች "በሾፌር መካኒክነት" በድምሩ ለ14 ሾፌሮች በአዲስ አበባ በምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡<br>• በ6 ወር ውስጥ በየዳይሬክቶሬቱ የተሰጡ ስልጠናዎች መረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት በ23 የተለያዩ ርዕሶች ላይ ለ153 ወንድ እና ለ123 ሴት በድምሩ ለ276 (በድግግሞሽ) አመራሮችና ሰራተኞች አጫጭር ስልጠናዎች መሰጠቱን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ | በቁጥር | 30 | 14 | 46.67 | |
| 2.3.3 | ቅድመ ሥራ ማስተዋወቂያ (Induction) ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ለአዲስ ቅጥር ሰራተኞች ስልጠና መስጠት | • | በቁጥር | 26 | 0 | 0 | ለአዲስ ሰራተኞች ቅድመ ሥራ ማስተዋወቂያ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ከህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ወደ መ/ቤታችን ከተመደቡ ሰራተኞች ጋር አብሮ ለመስጠት ስለታሰበ በዕቅዱ መሰረት አልተከናወነም፡፡ |
| 2.3.4 | ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ወጣት ባለሙያዎች በኢትዮጵያ | • በ2 ዙር ለ52 የመ/ቤቱ ሰራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ | በቁጥር | 52 | 21 | 40.38 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| | ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የአቅም ግንባታ ስልጠና ማመቻቸት | የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ21 ሰራተኞች ተሰጥቷል። | | | | | |
| 2.4 | የሰራተኞችን የውጤት ተኮር አፈፃፀም የተጠቃለለ ውጤት መረጃዎች አጠናክሮ መያዝ | • ከሀምሌ 1/2013-ታህሳስ 30/2014 ያለው የሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት በወቅቱ እንዲሞላ የመከታተልና ድጋፍ የማድረግ ስራ ተከናውኗል።<br>• የ160 ሰራተኞች የ6 ወር የስራ አፈፃፀም ተሞልቶ ተልኳል። | በቁጥር | 1 | - | 82.47 | ከ194 ሰራተኞች የ160 ሰራተኞች የስራ አፈፃፀም አፈፃፀም ተልኳል። ስራው 82.47 በመቶ ተከናውኗል። |
| 3 | **የግብዓት ዝግጅት** | | | | | | |
| 3.1 | የመ/ቤቱን የ2013 አመታዊ የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ሪፖርት እና የ2014 በ.ዓ የስራ መርሃ-ግብር ማዘጋጀት እና ለገ/ሚ መላክ | • የ2013 አመታዊ የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ሪፖርት እና የ2014 በ.ዓ የስራ መርሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለገ/ሚ ተልኳል። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 3.2 | የመ/ቤቱን የ2014 በጀት ዓመት የየሩብ ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀትና ለገ/ሚ መላክ | • የ2014 በጀት አመት የ1ኛው ሩብ ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለገ/ሚ ተልኳል። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 3.3 | የመ/ቤቱን የ2014 በጀት ዓመት የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት እና ማፀደቅ | • የስራ ክፍሎች የግዢ ፍላጎት በማሰባሰብ በመንግስት የግዢ መመሪያ መሰረት የመ/ቤቱን የግዢ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በበላይ ሃላፊ ፀድቆ ለግዥ ኤጀንሲ በሃርድ ኮፒ እና በሲስተም (EGP)ተልኳል።<br>• ቋሚ ዕቃዎች (ላፕቶፖች፣ ከለር ፕሪንተሮች) በማዕቀፍ ግዥ ተገዝተዋል። ቀሪ ግዥዎች በሂደት ላይ ይገኛሉ። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | የማዕቀፍ ግዥ በወቅቱ ባለማቅረባቸው ምክንያት በየስራ ክፍሉ የሚጠየቁ የግዥ ፍላጎቶች በወቅቱ ማድረስ አልተቻለም። |
| 3.4 | የመ/ቤቱን የ2014 በጀት ዓመት የሩብ ዓመት የግዥ ሪፖርት ማዘጋጀት | • የ2014 በጀት ዓመት የሩብ ዓመት የግዥ ሪፖርት ተዘጋጅቷል። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | | **ስትራቴጂክ ግብ 1፡- የአሰራር እና የአገልግሎት አሠጣጥ ስርዓትን ማጎልበት፤** (ክብደት 12) | | | | | |
| 1 | የሚኒስቴር መ/ቤቱን የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ማጎልበት | • የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2014 በ.ዓ የ1ኛው ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተልኳል።<br>• የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2014 በ.ዓ የ6 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቷል። | በቁጥር | 2 | 2 | 100 | |
| 2 | ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ክፍሎች እና ለተጠሪ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ማድረግ | | | | | | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 | ለመ/ቤቱ የሥራ ክፍሎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | • የበላይ አመራሩ በዘርፋቸው ስር ላሉ የስራ ክፍሎች ጋር ድጋፍና ክትትል አድርገዋል፡፡ | በቁጥር | 2 | 2 | 100 | |
| 2.2 | ለተጠሪ ተቋማት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | • ከተጠሪ ተቋማት (የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት፣ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲዩት እና የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን) ጋር በቅንጅት የሚከናወኑ ስራዎች ለየታ በማከናወን ለቀጣይ ጊዜያት በተሻለ መስራት የሚቻልበት ሁኔታዎች ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ | በቁጥር | 2 | 2 | 100 | |
| 3 | የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ስራዎችን መከታተል | | | | | | |
| 3.1 | የመ/ቤቱን አመራርና ሰራተኞች ሃብትና ንብረት ማስመዝገብ | • የመ/ቤቱ አጠቃላይ ሰራተኞች የሃብት ምዝገባ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ | በቁጥር | 30 | 185 | 100 | |
| 3.2 | ተቋሟዊ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት | • ተቋሟዊ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ከፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ስትራቴጂክ ዕቅዱ ቀርቶ በመ/ቤቱ የስራ ክፍሎች ላይ የአሰራር ጥናት ተካሂዶ ሪፖርት እንዲዘጋጅ ተጠይቋል፡፡<br>• በዚህም የግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት እና በሠው ሀብት አስተዳደርና ልማት ዳይሬክቶሬት ላይ የአሰራር ጥናት ተካሂዶ ሪፖርቱ ለስራ ክፍሉ ሃላፊ፣ ለበላይ ሃላፊዎችና ለፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተልኳል፡፡<br>• በቀጣይ በስምሪትና በነዳጅ አጠቃቀም ላይ የአሰራር ጥናት ለማድረግ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 3.3 | የስነ-ምግባር መመሪያ/ኮድ ላይ ለተቋሙ አመራርና ሰራተኞች ስልጠና መስጠት/ግንዛቤ ማስጨበጥ | • ለተቋሙ ሃላፊዎች የስነ-ምግባር መመሪያ/ኮድ ላይ የ2 ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 3.4 | የስነ-ምግባር መመሪያ/ኮድ ተግባዊነትን መከታተል እና አስቸኳይ የሙስና መከላከል ተግባራትን ማከናወን | • የስነ-ምግባር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡<br>• አስቸኳይ የሙስና መከለከል ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 3.5 | ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን በመለየት ጥናት ማካሄድ እና የተለዩ የአሰራር ክፍተቶችን ለመቅረፍ የሚሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ | • በአስቸኳይ ሙስና መከላከል የተቋሙን ሃብት አላግባብ እንዳይባክን ተደርጓል፡፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |

የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት
የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 3.6 | ለመ/ቤቱ ሰራተኞች የስነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስናን ስለመከላከል ስልጠና መስጠት | • ለመ/ቤቱ 98 ሰራተኞች በስነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስናን ስለመከላከል የአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ | በቁጥር | 3 | 1 | 33.3 | |
| 3.7 | የፀረ-ሙስና ቀንን ማክበር | • የተቋሙ 118 ሰራተኞች በተገኙበት የፀረ-ሙስና ቀን ተከብሯል፡፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 4 | የመንግሥት የፋይናንስ አሰራር ሥርዓትን በመከተል የአገልግሎት አሠጣጥ ሥርዓትን ማጎልበት | | | | | | |
| 4.1 | የፋይናንስ መመሪያና ደንብን ተከትሎ ክፍያዎችን መፈጸም | • የፋይናንስ ሥርዓት በማጠናከር የመንግስት የፋይናንስ መመሪያዎችን የተከተሉ በጥሬ ገንዘብ ዕቅድ ላይ የተመሠረቱ ክፍያዎች ተፈፅመዋል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 4.2 | የ2014 በጀት ዓመት የሚኒስቴር መ/ቤቱን የፋይናንስ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በኢፍሚስ በየወቅቱ ማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው አካላት መላክ | • ከሐምሌ እስከ ህዳር ወር 2014 ዓ.ም ያለው ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ለገ/ሚ ተልከዋል፡፡<br>• የታህሳስ ወር 2014 ዓ.ም የሂሳብ ሪፖርት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ | በቁጥር | 6 | 5 | 83.3 | |
| 5 | የውስጥ ኦዲት ሥራዎችን ማከናወን | | | | | | |
| 5.1 | የ2013 በጀት ዓመት የመዝጊያ ቆጠራ ማከናወን | • የ2013 በጀት ዓመት የመዝጊያ ቆጠራ ተከናውኗል፡፡<br>• የኦዲት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ሠራተኞች ተሰጥቷል፡፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 5.2 | የ2013 በጀት ዓመት የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት | • የ2013 በጀት ዓመት የ4ኛው ሩብ ዓመት የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡<br>• የ2013 በጀት ዓመት የ4ኛው ሩብ ዓመት የፋይናንስና የንብረት ኦዲት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለመ/ቤታችን ሲቀርብ በግልባጭ ለገንዘብ ሚ/ር እንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ተልኳል፡፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 5.3 | የ2014 በጀት ዓመት የየሩብ አመት የፋይናንስና የንብረት ኦዲት ማድረግ | • የ2014 በጀት ዓመት የ1ኛው ሩብ ዓመት የፋይናንስና ንብረት ኦዲት የተደረገ ቢሆንም ሪፖርቱ ተጠናቆ አልወጣም፡፡ | በቁጥር | 1 | 0.75 | 75 | |
| 5.4 | በኦዲት ግኝቶች ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ክትትል ማድረግ | • በ2013 በጀት ዓመት የተገኙ ግኝቶች ስለመታረማቸው ክትትል ተደርጎ ለመ/ቤታችንና ለገንዘብ ሚ/ር እንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ተልኳል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 6 | የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ | | | | | | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 6.1 | የተቋሙን ሴት ሰራተኞች በራስ የመተማመንና የአመራር ብቃትና ክህሎት ለማጎልበት የሚያስችል ስልጠና መስጠት | | በቁጥር | 1 | 0 | 0 | የስልጠና በጀት ባለመኖሩ ምክንያት በዕቅዱ መሰረት ስልጠና አልተሰጠም። በቀጣይ የስልጠና በጀት ሲፈቀድ የሚሰጥ ይሆናል። |
| 6.2 | የህፃናት ማቆያ ግንባታን ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን መከታተል | • የህፃናት ማቆያ ግንባታ የሚውል በጀት ከገንዘብ ሚ/ር ተመድቧል።<br>• 30 ሕጻናትን ለማስተናገድ የሚያስችል ሕንጻ ለመስራት ዝግጅቱ ተጠናቋል። | በመቶኛ | 40 | 40 | 100 | |
| 6.3 | የተቋሙ ሠራተኞች ያታዊ ጥቃትና ኤች አይ ቪኤድስ ላይ ወቅታዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ | • ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር፣ ከሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ባለሙያዎች ተጋብዘው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሠጥቷል።<br>• የፀረ-ጾታዊ ጥቃት ቀን ምክንያት በመድረግ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በደረሰው ችግር ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉና የጾታ ጥቃት ለደረሰባቻዉ ሴቶችና ሕጻናት የተቋሙን ሠራተኞች በማስተባበር በዓይነት 230 የሕጻናትና የአዋቂ አልባሳት በገንዘብ 6,590 (ስድስት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ብር) ድጋፍ ተሰብስቦ የንጽህና መጠበቂያዎችና የታሸገ ደረቅ ምግቦች ተገዝተው ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተልኳል። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 6.4 | በቅጥር፣ በደረጃ እድገትና በትምህርትና ስልጠና ምልመላ ላይ ለሴቶች ልዩ ድጋፍ (Affermative action) ተግባራዊ መደረጉን መከታተል | • ለተቋሙ ሴት ሰራተኞች በትምህርትና ስልጠና ምልመላ ላይ ልዩ ድጋፍ (Affirmative action) ተግባራዊ መደረጉን ክትትል ተደርጓል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 7 | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና የዕውቀት ማኔጅመንት ሥራዎችን ማጎልበት | | | | | | |
| 7.1 | በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት የኢ-ሰርቪስ አገልግሎት ለማስጀመር ድጋፍ ማድረግ | • የኢ-ሰርቪስ አገልግሎትን በተሻሻለው አደረጃጀት መሰረት ለማስጀመር የስራ ፍሰታቸውን በመከለስ ለአገልግሎት ዝግጁ ተደርጓል።<br>• በኢ-ሰርቪስ ዙርያ ለ33 ሰራተኞች የአጠቃቀም ስልጠና እና ለ8 አይቲ ባሞያዎች ቴክኒካል ስልጠና ተሰጥቷል። | በመቶኛ | 6 | 6 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 7.2 | የገመድ አልባ ኢንተርኔት (WiFi) አገልግሎት መስጠት | • የገመድ አልባ ኢንተርኔት (Wi-Fi) አገልግሎት እየተሰጠ ነው። | በመቶኛ | 50 | 50 | 100 | |
| 7.3 | የመ/ቤቱን የኤሌክትሮኒክ ሜይል ሲስተምን ማስተዳደር | • የመ/ቤቱን የኤሌክትሮኒክ ሜይል ሲስተምን የማስተዳደር ስራ እየተሰራ ነው። | በመቶኛ | 50 | 50 | 100 | |
| 7.4 | የመ/ቤቱን ድረ-ገፅ ማስተዳደር | • የመ/ቤቱ ድረ-ገፅ የማልማት ስራ ተጠናቋል።<br>• ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት አልጀመረም። ዜናና ሰነዶች እየተጫኑበት አይደለም። | በመቶኛ | 50 | 0 | 0 | |
| 7.5 | የተቋሙን ስብሰባዎች ቨርቹዋል ማድረግ | • ቨርቹዋል ስብሰባዎች ሲደረጉ ቴክኒካል ድጋፍ እየተደረገ ነው። | በመቶኛ | 50 | 50 | 100 | |
| 7.6 | የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ ስርዓት ትግበራን ማጠናከር | • የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ ስርዓት ትግበራን ለማጠናከር እገዛ እየተደረገ ነው። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 7.7 | የአይቲ ድጋፍ ማድረግ እና የሲስተምና ኔትወርክ አስተዳደር ሥራዎችን ማከናወን | • ከየስራ ክፍሉ የተጠየቁ የአይቲ (IT) ድጋፍ ጥያቄዎች ተስተናግደዋል። | በመቶኛ | 50 | 50 | 100 | |
| 7.8 | የቤተ-መፅሀፍት አገልግሎት መስጠት (የንባብ አገልግሎት መስጠት፣ ማዋስ፣ ማስመለስ ወ.ዘ.ተ) | • የቤተመፅሀፍት አገልግሎት ለማስጀመር ክትትል እየተደረገ ነው። | በመቶኛ | 100 | 0 | 0 | |
| 7.9 | ሌሎች ወቅታዊና ተጨማሪ ሥራዎችን ማከናወን (D-MRS ትግበራን ማጠናከር) | • በፌዴራል ተቋም ደረጃ የዲጂታል ክትትልና ግምገማ ሲስተም (D-MRS) ተግባራዊ በመደረጉ የተቋማቱ እቅድ ከ 2,700 በላይ ቁልፍ መለኪያዎች ወደ ሲስተሙ ኢንኮድ ተደርገዋል:<br>• በተጨማሪም ተቋማት ሪፖርታቸውን በሲስተሙ እንዲልኩ ቴክኒካል ድጋፍ እየተደረገ ነው። | በመቶኛ | 50 | 50 | 100 | |
| 8 | የህዝብ ግንኙነትና የኮሚኒኬሽን ስራዎችን ማሳደግ | | | | | | |
| 8.1 | የመ/ቤቱን ተልእኮ ለማሳደግ የተሰባሰቡ መረጃዎችን በመቀመር እንደ ታዳሚው ባህሪ አዋጭ በሆነው የመገናኛ ስልት የተመረጡ መልእክቶችን ማደራጀትና ማሰራጨት | | | | | | |
| 8.1.1 | በተሰባሰበው መረጃ መሰረት ዜናና አርቲክል ማዘጋጀት | • በ6 ወራት ውስጥ በ3 ጋዜጣዎች ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱን በተመለከተ 3 አርቲክሎች ታትመዋል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 8.1.2 | በማህበራዊ ድረ-ገፅ አማካኝነት መረጃ ማሰራጨት፣ የማህበራዊ ድረ-ገፅ ተከታዮቻችንን መጨመር | • ማህበራዊ ድረ-ገፅ አማካኝነት በአማካኝ 35 ዜናዎች ተዘጋጅተዋል፡፡<br>• 8,400 የትዊተር ተከታዮችንና 16,700 የፌስቡክ ተከታዮችን አፍርቷል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 8.1.3 | በህትመትና መገናኛ ብዙሃን በመጠቀም ወቅታዊ መልእክቶችን ማስተላለፍ | • የተለያዩ ወቅታዊ መረጃዎች ተላልፈዋል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 75 | 75 | |
| 8.2 | የውይይት መድረኮች፤ በመምራትና በማስተባበር ውጤታማ የግብረ መልስ ስርአት በመዘርጋት ክህሎትንና እውቀትን በማሳደግ አቅምን ማጎልበት | | | | | | |
| 8.2.1 | ጋዜጣዊ መግለጫዎች መስጠት | • | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | በተደራራቢ የስራ ጫና ምክንያት ጋዜጣዊ መግለጫዎች አልተሰጡም፡፡ |
| 8.3 | የሚኒስቴር መ/ቤቱን የበጀት አጠቃቀም መረጃዎች ተደራሽ በማድረግ የፋይናንስ ግልፀኝነትና ተጠያቂነትን ማስፈን | • የመ/ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት የ1ኛው እና የ2ኛው ሩብ ዓመት የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት ተደራሽ ተደርጓል፡፡ | በቁጥር | 2 | 2 | 100 | |
| 9 | የሚኒስቴር መ/ቤቱን የንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ስራዎችን ማስተዳደር | | | | | | |
| 9.1 | ለሰራተኞችና ለተጠቃሚዎች ምቹ የስራ ቦታ ለመፍጠር አካባቢን ማስዋብና መንከባከብ | • የመ/ቤቱን ምድረ-ግቢ ለሰራተኞች ምቹ እና አይን ሳቢ ለማድረግ አትክልቶችን የመንከባከብና የማስዋብ ስራዎች ተሰርተዋል፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 9.2 | የአጥርና የግቢ ዕድሳት ማድረግ | • የግቢ እድሳቱን በተመለከተ የአበባ መትከያ በታዎች ተገንብተው ለአበባዎች እንክብካቤ እየተደረገ ይገኛል፡፡ | በመቶኛ | 50 | 25 | 50 | ስራው በዲዛይን ማሻሻያ ምክንያት የተራዘመ በመሆኑን በዕቅዱ መሰረት አልተከናወነም፡፡ |
| 9.3 | የአረንጓዴ አሻራ ልማት ማስቀጠል | • አረንጓዴ አሻራ ለማሳረፍ የመ/ቤቱ አመራሮችና ሰራተኞች በእንጦጦ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም አካሂደዋል፡፡<br>• በተጨማሪም የመ/ቤቱ የበላይ አመራሮችና የስራ ሃላፊዎች በሸዋ ሮቢ ከተማ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም አከናውነዋል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 9.4 | ቀልጣፋና ፈጣን የተሽከርካሪ ስምሪት፣ መረጃና ደህንነት መጠበቅ | • የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሰርቪስ ጊዜን ጠብቆ ሰርቪስና ጥገና እንዲገቡ ተደርጓል፡፡<br>• ከስራ ክፍሎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሰረት የተሽከርካሪ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 9.5 | የንብረት አያያዝና አስተዳደርን ስርዓትን ማጎልበት | • ተገዝተው የሚገቡ ቋሚ/አላቂ ንብረቶች በIFMIS ወጪ ገቢ ተሰርቷል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 9.6 | የመ/ቤቱን ንብረቶች ማስወገድና አመታዊ ቆጠራ ማድረግ | • በስጦታ የማስወገድ ዘዴን በመጠቀም;<br>• ለሸዋ ሮቢት ት/ቤቶች<br>• የአካል ጉዳተኛ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ<br>• ለሜቆዶንያ የተለያዩ ንብረቶች በስጦታ ተሰጥቷል።<br>• በመ/ቤቱ በድሮው ህንፃ የነበሩ መጋረጃዎች ለውስጥ ሰራተኞች ተሸጠው ወደ መንግስት በጀት ፈሰስ ተደርጓል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| **ስትራቴጂክ ግብ 2፡- ኢኮኖሚውን በረዥም ጊዜ ዕይታ በመምራት ፈጣን ፍትሐዊና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ ማገዝ፤ (ክብደት 12)** | | | | | | | |
| 1 | የ30 ዓመት የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት | | በመቶኛ | 100 | 35 | 35 | |
| 1.1 | ለልማት ዕቅዱ ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ | • ለልማት ዕቅዱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች እየተሰባሰቡ ይገኛሉ። | በመቶኛ | 100 | 40 | 40 | |
| 1.2 | የጥናት ውጤቶችን የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮዎችን ማሰባሰብና መቀመር | • የጥናት ውጤቶች እየተሰበሰቡ ይገኛሉ። | በመቶኛ | 100 | 20 | 20 | |
| 2 | የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ፣ ማኑዋል እና ቼክሊስቶች ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ማዘጋጀት | | | | | | |
| 2.1 | የስፓሻል ፕላን ማዕቀፍ ማዘጋጀት | • የስፓሻል ፕላን ማዕቀፍ ይዘቶች እንዲሁም የድርጊት መርሃግብር ተዘጋጅቷል።<br>• ለማዕቀፉ ዝግጅት የሚያስፈልጉ ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብሰብዋል፤ ውርክ ሾፕ ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል። | በመቶኛ | 50 | 40 | 80 | |
| 2.2 | የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ ማዘጋጀት | • የልማት ዕቅድ ፅንሰ ሃሳብ ተዘጋጅቷል። | በመቶኛ | 50 | 50 | 100 | |
| 2.3 | የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት ቼክሊስቶችን ማዘጋጀት | • የ10 ዓመቱን የልማት ዕቅድ ተፈፃሚ ለማድረግ የአንድ አመት ዕቅድ በማውረድና የአንድ አመቱን በሩብ ዓመት ለመከፋፈልና ለማዘጋጀት የሚረዳ ቼክሊስት ተዘጋጅቶ ወደ ተቋማት ተልኳል። | በመቶኛ | 25 | 25 | 100 | |
| 3 | የአንድ አመት እና የሶስት አመት የአጭር ዘመን የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት | | | | | | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 3.1 | ከዘርፎች የፕሮግራም በጀትና ውጤት ጋር የተጣጣመ የ2014 በጀት ዓመት ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት | • የ2014 በጀት ዓመት ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቷል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 3.2 | የ3 ዓመት (2014-2016 በጀት ዓመት) የዕቅድ ሰነድ ማዘጋጀት | • የማክሮ ፍሬም ወርክ ሰነድ ተዘጋጅቷል። | በመቶኛ | 100 | 5 | 5 | አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ለማድረግ አጠቃላይ የልማት ዕቅዱን ክለሳ ለማድረግ ስለታሰበ ከዚህ ጋር ተያይዞ በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል። |
| 4 | የ2014 በጀት ዓመት እና የ3 ዓመት (2014-2016 በጀት ዓመት) የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ማዘጋጀት | • የ2014 በጀት ዓመት እና የ3 ዓመት (2014-2016 በጀት ዓመት) የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 5 | የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ማስተግበሪያ ስልቶች ተጨማሪ ሰነድ ማዘጋጀት | | | | | | |
| 5.1 | የሰው ሃብት ልማት ዕቅድ ማዘጋጀት | • የሰው ሀብት ልማት ዕቀዱ መሰረታዊ ይዘቶች እና የእቅዱ ዋና ዋና የትኩረት መስኮች ተለይተዋል፤ተሞክሮዎች ተቀምረዋል። | በመቶኛ | 100 | 50 | 50 | |
| 5.1.1 | የሀገሪቱን የሥነ ህዝብ ተለዋዋጭ ባህሪያትን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የዘርፎች የሰው ሀይል ፍላጎትን ከልማት ዕቅድ ጋር እንዴት አስተሳስሮ ማስተግበር እንደሚቻል የሚያሳይ መነሻ ጽንስ ሀሳብ ማዘጋጀት | • Annotated outline ተዘጋጅቷል። | በመቶኛ | 100 | 50 | 50 | |
| 5.1.2 | በጽንሰ ሀሳቡ ላይ ከዘርፍ አስፈጻሚ መ/ቤቶች፣ ከግሉ ዘርፍ፣ ከልማት አጋሮች እና ሌሎች ከስራ ፈጠራ ጋር በተያያዘ ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማድረግ | • ለውይይት የሚሆን የመነሻ ጽንሰ ሀሳብ ተዘጋጅቶ ባለመጠናቀቁ ውይይቱ አልተከናወነም። | በቁጥር | 4 | 0 | 0 | |
| 5.1.3 | የሌሎችን ሀገሮች የሰው ሀይል ፍላጎትን ከስነ ህዝብ ባህሪያት አንጻር በመቃኘት ከልማት ዕቅድ ጋር አስተሳስረው ያስተገበሩበትን ምርጥ ተሞክሮችን መቀመር | • የሌሎች ሃገሮች ተሞክሮ ተቃኝቷል። | በመቶኛ | 100 | 50 | 50 | |
| 5.2 | ለልማት ዕቅዱ ማስፈጸሚያ የሚሆን የፋይናንስ ፍላጎት ፕላን ማዘጋጀት | | | | | | |
| 5.2.1 | ቴክኒካልና ስትሪንግ ኮሚቴዎች ማቋቋም | • ቴክኒካል ኮሚቴ ተቋቁሟል። | በቁጥር | 2 | 1 | 50 | የስትሪንግ ኮሚቴ አልተቋቋመም |
| 5.2.2 | የልማት ፋይናንስ ዕቅድ መነሻ ሀሳብ በማዘጋጀት ለውይይት ማቅረብ | • መነሻ ሀሳብ ተዘጋጅቷል። | በመቶኛ | 100 | 50 | 50 | |
| 5.2.3 | ለልማት ዕቅዱ ማስፈጸሚያ የሚሆን የፋይናንስ ፍላጎት | • የፋይናንስ ፍላጎት በተቀመጠው አግባብ የመለየት ስራ | በመቶኛ | 100 | 0 | 0 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| | በወጪ መጠንና በምንጭ እንዲሁም በዶላርና በብር በመለየት የዕቅድ ሰነድ ማዘጋጀት | አልተከናወነም። | | | | | |
| 6 | የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ማስተዋወቅ | | | | | | |
| 6.1 | በልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ በልማት ፕሮግራም ቀረጻ እና ለልማት ዕቅድ በሚያገለግሉ ስልቶች ላይ ለተቋሙ ባለሙያዎች፣ ለፌደራል አስፈጻሚ ባለሙያዎች እና ለክልሎች ስልጠና መስጠት | • በተቋማት ጥያቄ መሰረት በተናጥል የማስተዋወቅ እና ስልጠና የመስጠጥ ተግባራት ተከናውነዋል። | በቁጥር | 4 | 4 | 100 | በስራ መደራረብ ምክንያት በዕቅዱ መሰረት ባይከናወንም በተለያዩ መድረኮች ማለትም በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማህበር መድረክ፣ በክልሎች በድሬደዋ፤ ሀረሪ፣ ሶማሌ እና ለተለያዩ ሲቪክ ማህበራት ስልጠና ተሰጥቷል። |
| 6.2 | የ10 ዓመት የልማት ዕቅዱን ማስተዋወቅ | • የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ለፌደራልና ለክልል ተቋማት ተሰራጭቷል። | በቁጥር | 5 | 5 | 100 | |
| 7 | የማክሮ ኢኮኖሚውን ወቅታዊ ሁኔታ በየጊዜው በመከታተል መንግስትንና ባለድርሻ አካላትን ማሳወቅ | | | | | | |
| 7.1 | የ2013 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የማክሮ ኢኮኖሚ ዋና ዋና ግቦች አፈጻጸምን የሚያሳይ ሪፖርት ማዘጋጀት፣ ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት | • የ2013 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የማክሮ ኢኮኖሚ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ሰነድ ለማዘጋጀት አስፈላጊ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው የማክሮ ኢኮኖሚ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 7.2 | የ2014 የ1ኛው፣የ2ኛው እና የ3ኛው ሩብ ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት፣ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት | • የ2014 የ1ኛው ሩብ ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ሪፖርት አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ሰነድ ለማዘጋጀት አስፈላጊ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው የማክሮ ኢኮኖሚ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን የሪፖርት ዝግጅት እየተከናወነ ይገኛል። | በቁጥር | 1 | 0.9 | 90 | |
| 7.3 | የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ለውጥ አዝማሚያዎችን ላይ ጥናት ማከናወን፤ ለዋጋ ጭማሪ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች የእሴት ሰንሰለትን /Inflation Value-Chain Analysis/ መሰረት ያደረገ ትንታኔ ማድረግ | • ብሔራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ የዋጋ ግሽበት በኢኮኖሚዉ ላይ እያደረሰ ያለዉን ጫና ለመቆጣጠር የሚያስችል ፕሮግራም ነድፎ ተግባራዊ ለማድረግ ባስቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ለዋጋ ንረት ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች ላይ ትንታኔ የሚያደርጉና የመፍትሄ ሃሳቦችን የሚያስቀምጡ ጥናቶችን እንዲያካሄዱ ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ የሚኒስቴር መ/ቤቶች አቅጣጫ ሰጥቷል።<br>• በመሆኑም የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ስራውን የማስተባበር ሃላፊነቱን | በመቶኛ | 50 | 50 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| | | በመውሰድ የተለያዩ ቴክኒካል ስራዎችን በመስራት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር በተያያዘ በዋጋ ግሽበት ዙሪያ እና በእሴት ሰንሰለት ጥናት በማጥናት የመነሻ ጥናት ቀርቧል፡፡<br>● መረጃዎችን የመሰብሰብ ስራዎችና የማደራጀት ስራዎች እየተከወኑ ይገኛሉ፡፡ | | | | | |
| **ስትራቴጂክ ግብ 3፡- የብሔራዊ የልማት ዕቅድና የልማት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ክትትልና ግምገማን ማጠናከር፤ (ክብደት 10)** | | | | | | | |
| 1 | የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) የማክሮ እና የዘርፍ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በመገምገም የተጠቃለለ የአምስት ዓመት አገራዊ የግምገማ ሪፖርት በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቅጅዎች በገለልተኛ አማካሪዎች በመታገዝ ማዘጋጀት | ● ቀደም ብሎ በተዘጋጀው የሥራ መዘርዝር መሠረት በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም በኩል ማስታወቂያ ወጥቶ አማካሪዎች አመልክተዋል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 58 | 58 | አማካሪዎቹን አወዳድሮ የመምረጥ እና አስፈላጊው በጀት የመመደብ ስራ ስላልተከናወነ ሥራው አልተጀመረም፡፡ ከዚህ አኳያ በቀጣይ ለመረጃ ያክል በውስጥ አቅም የዳሰሳ ሪፖርት ለማዘጋጀት የሞከራል፡፡ |
| 2 | የአስር ዓመቱ (2013-2022) የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የተቀናጀና ወጥ የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት | ● የአስር ዓመቱ (2013-2022) የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የተቀናጀና ወጥ የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት ለመዘጋጀት ከዘርፍ አስፈጻሚ መ/ቤቶች መረጃዎች በመሰብሰብ የዘርፍ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 2.1 | የኢኮኖሚ ዘርፎች የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት | ● የኢኮኖሚ ዘርፎች (የግብርና፣ የአካባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለውጥ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ፣ የኢንቨስትመንት፣ የባህልና ቱሪዝም እንዲሁም የማዕድንና ነዳጅ ዘርፎች) የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 2.2 | የማህበራዊ ዘርፎች የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት እንዲሁም የስርዓተ ምግብ ጉዳይ፣ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ እና ሌሎች የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች መካተታቸውን ማረጋገጥ | ● የማህበራዊ ዘርፎች (የማህበራዊ እና ሰራተኛ ዘርፍ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ ንዑስ ዘርፍ፣ የጤና ዘርፍ፣ የአጠቃላይ ትምህርት፣ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ እና የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ) የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 2.3 | የመልካም አስተዳደርና ሰላም ዘርፍ የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት | ● የመልካም አስተዳደርና ሰላም ዘርፍ (የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የፍትህ ሚኒስቴር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የሰላም ሚኒስቴር) የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 2.4 | የመካከለኛና ትላልቅ የመሠረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ደረጃ የሚያሳይ የ2013 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ሪፖርት ማዘጋጀት | • 383 የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ 24 የግድብና መስኖ ፕሮጀክቶች፣ 21 የኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማከፋፊያ ፕሮጀክቶች፣ 14 የኢንዱስትሪያል ፓርክ ፕሮጀክቶች፣ 6 የስኳር ፕሮጀክቶች፣ 3 የባቡር ፕሮጀክቶች እና 11 የፌዴራል የመንግስት ቢሮ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡<br>• ሪፖርቱም ሲዘጋጅ የፊዚካልና የፋይናንስ አፈፃፀም፣ ፕሮጀክቶች በመዘግየታቸው ምክንያት ከአስከተሉት ወጪ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ከአጋጠሙ ችግሮችና ከተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ አንፃር ትንተና ተካሂዶ አንድ የትንተና ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡<br>• በተጨማሪም የመሰረተ ልማት ዘርፍ (የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ፣ የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ) የ2013 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የአፈፃፀም ሪፖርት ከተቀመጠው የአስር ዓመት ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ አንፃር ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 3 | በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት ትግበራ ወቅት ደካማ አፈጻጸም ባሳዩ በተመረጡ ፕሮግራሞች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | | | | | | |
| 3.1 | በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የጤና ዘርፍ ዓመታዊ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ መስክ ምልከታ በማካሄድ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ | • በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የጤና ዘርፍ ዓመታዊ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ መስክ ምልከታ ለማካሄድ ቢጋር/TOR ተዘጋጅቷል፡፡ | በመቶኛ | 25 | 25 | 100 | |
| 3.2 | በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የኢኮኖሚ ዘርፎች ዓመታዊ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ መስክ ምልከታ በማካሄድ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ | • በመስክ ምልከታ ክትትል ሊደረግባቸው የሚገቡ የኢኮኖሚ ዘርፎች የልማት ዕቅዶችን የመለየት እና የክትትልና ግምገማ ቼክ ሊስት የማዘጋጀት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ | በቁጥር | 1 | - | - | በቀጣይ በዕቅዱ መሰረት የሚከናወ ይሆናል፡፡ |
| 3.3 | የመካከለኛና ከፍተኛ የመሠረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም በመስክ መመልከትና ድጋፍ ማድረግ | • በሦስት ዘርፎች ማለትም በግድብና መስኖ፣ በኢነርጂ እና በመንገድ ዘርፍ አራት ፕሮጀክቶች ማለትም በካሊድ ዲጆ ግድብና መስኖ፣ አዳማ 2- 230/132/15 ኪሎ ቮልት የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ፣ መልካሳ-ሶደሬ-ኑራሄራ-መተሀራ መንገድ እና የኢተያ-ሮቤ አገናኝ መንገድ ፕሮጀክቶች የመስክ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| | | • በመስክ መልከታውም ከተለዩት ችግሮች መካከል የወሰን ማስከበርና ካሳ ክፍያ ችግር፣ የተቋራጮች አቅም ውስንነት፣ የግብዓት እጥረት፣ የፀጥታ ችግር፣ የቅንጅት ችግር፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ በአግባቡ አለማሳተፍ፣ የፕሮጀክቶች መዘግየትና ወጪ መጨመር እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ እጥረት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡<br>• በመስክ መልከታውም የተለዩ ችግሮች በሚፈቱበት አግባብ ላይ የፕሮጀክቱ ወሳኝ አካለት (የፕሮጀክቱ ባለቤት፣ አማካሪና ተቋራጭ) እና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በውይይቱ መድረክ ላይ የየድርሻቸውን እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡<br>• በተመሳሳይ የፌዴራል ተቋማትን ጣልቃ ገብነት የሚፈልጉ የፕሮጀክቶች ችግሮችና ጉዳዮች ላይም የተቋማት የ100 ቀናት ዕቅድ አፈፃፀም በሚገመገምበት ወቅት ችግሮች በሚፈቱበት አግባብ ላይ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ | | | | | |
| 4 | የኢኮኖሚ ዘርፎችን የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2014 በጀት ዓመት አፈፃፀምን መከታተል | • የኢኮኖሚ ዘርፎች (የግብርና፣ የአካባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለውጥ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ፣ የኢንቨስትመንት፣ የባህልና ቱሪዝም እንዲሁም የማዕድንና ነዳጅ ዘርፎች) የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶችን በቀጣይ በ2014 በጀት ዓመት አፈፃፀም ላይ እንዳይደገሙ ለማድረግ ተገቢውን ግበረመልስ ተዘጋጅቷል፡፡<br>• በተጨማሪም የኢኮኖሚ ዘርፎች የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው እና የሁለተኛው ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 5 | ከመልካም አስተዳደርና ሰላም ዘርፍ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት Baseline የሌላቸው የአፈጻጸም አመልካቾች እንዲሟሉ ማድረግ | | በመቶኛ | 60 | 0 | 0 | ከተቋማቱ አስፈላጊውን ትብብር ማግኘት ባለመቻሉ እንዲሁም ለስራው ትኩረት ባለመስጠታቸው በዕቅዱ መሰረት ማከናወን አልቻለም፡፡ |
| 6 | የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ፕላን የአፈጻጸም አመልካቾችን ማዘጋጀት | • የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ፕላን የአፈጻጸም አመልካቾችን የማዘጋጀት ስራ ተጠናቋል፡፡ | በመቶኛ | 30 | 100 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 7 | የመካከለኛና ከፍተኛ የመሠረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ደረጃ የሚያሳይ የሩብ ዓመት የተጠቃለለ ሪፖርት ማዘጋጀት | • የፕሮጀክቶች አፈፃፀም በሦስቱ የክትትል አግባቦች ማለትም በሪፖርት፣ በገፅ-ለገፅ እና በመስክ በሩብ ዓመቱ ክትትል ተደርጓል።<br>• የ2014 በጀት ዓመት የ1ኛ ሩብ ዓመት የተጠቃለለ የመሰረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ሪፖርት ከማዘጋጀት አንፃር የመንገድ፣ የግድብና መስኖ፣ የኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማከፋፊያ፣ የኢንዱስትሪያል ፓርክ፣ የስኳር ልማት፣ የባቡር መስመር ዝርጋታ፣ እና የፌዴራል የመንግስት ቢሮ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም የፕሮጀክቶች የፊዚካልና ከፋይናንስ አፈፃፀም፣ ፕሮጀክቶች በመዘግየታቸው ምክንያት ከአስከተሉት ወጪ፣ በበጀት ዓመቱ ከአጋጠሙ ችግሮችና ከተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ አንፃር ትንተና ተካሂዶ አንድ ትንተና ሰነድ ተዘጋጅቷል።<br>• ከዚህም አኳያ ከተለዩት ችግሮች መካከል የዲዛይንና የአዋጭነት ችግር፣ የመሰን ማስከበርና የካሳ ክፍያ ችግር፣ የግብዓት ችግር (የሲሚንቶ፣ ብረት….ወዘተ) የተቋራጮች የአቅም ውስንነት፣ የቅንጅት ችግር እና ሌሎችም ተመሳሳይ ችግሮች ተለይተው ችግሮች በሚፈቱበት አግባብ ላይ ምክረ- ሃሳብ ቀርቧል። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 8 | በመሠረተ ልማትና በልማት ፕሮጀክቶች ፕላን አፈፃፀም ዙሪያ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ | | | | | | |
| 8.1 | የተዘጋጀው የፕሮጀክቶች የክትትልና ግምገማ ስርዓት ሠነድ የመጨረሻ ቅርፅ እንዲይዝ ማድረግና አፈፃፀሙን መከታተል | • የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም፡-<br>  • ከቅድመ-ትግበራ ስርዓት፤<br>  • ከፕሮጀክቶች ክትትል ስርዓት (ከዴስክ ሪቪውና ከመስክ ክትትል አንፃር፤<br>  • ከፕሮጀክቶች ግምገማ ስርዓት (ከቅድመ-ትግበራ፣ ከአጋማሽ ዘመን ግምገማ፣ ከመጨረሻ ዘመን ግምገማ እና ከፕሮጀክቶች ስኬትና ፋይዳ ግምገማ) ፤<br>  • ተሞክሮዎችን ከመቀመርና ተደራሽ ከማድረግ እንዲሁም ከአስቻይ ሁኔታዎች ማለትም ከቅንጅታዊ አሰራር፣ ከአቅም ግንባታ እና ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አንፃር | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| | | • በመከታተልና በመገምገም አፈፃፀማቸውን ማሻሻል የሚያስችል የፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ የአሰራር ስርዓት ሠነድ ተዘጋጀቶና በየደረጃው ግብዓት ተሰጥቶበት የመጨረሻ ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጎ ቀርቧል። | | | | | |
| 8.2 | የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ለመከታተል፣ ለመገምገምና መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ቋት እንዲበለፅግ ማድረግ | • የሥራውን ንድፈ-ሃሳብ የሚያሳይ የሥራው ዳራ፣ የችግሩ ስፋትና ጥልቀት፣ የሥራው ዓላማና ወሰን፣ ዝርዝር ተግባራትና የሚጠበቅ ውጤት፣ የመረጃ ቋቱ የሚመራበትና የሚተዳደርበት አግባብ እንዲሁም ለሥራው የሚያስፈልገው ዝርዝር ወጪ ተዘጋጅቶ ለዘርፉ ቀርቦ አቅጣጫ እየተጠበቀ ይገኛል። | በመቶኛ | 25 | 20 | 80 | |
| 9 | የዘላቂ የልማት ግቦችን እና የአፍሪካ አጀንዳ 2063 አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት | • ለ76ኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ግብዓት የሚሆን የተጠቃለለ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈጻጸም ተዘጋጅቶ ቀርቧል።<br>• የአፍሪካ የልማት አጀንዳ (አጀንዳ 2063) የመጀመሪያው 10 ዓመት ትግበራ ሁለተኛው ዙር የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ቀርቧል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| **ስትራቴጂክ ግብ 4፡- ብሔራዊ የልማት ዕቅድ ዝግጅትና የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ማጎልበት፤ (ክብደት 10)** | | | | | | | |
| 1 | በዳሰሳ ጥናት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም ግንባታ ተግባራትን ማከናወን | | | | | | |
| 1.1 | ለሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም ግንባታ ግብዓት የሚሆን ጥናት ማካሄድ | • ከተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት አድን ድርጅት ጋር በመሆን ሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም ዝግጁነት የዳሰሳ ጥናት በመካሄድ ላይ ሲሆን ረቂቅ ጥናቱ ተዘጋጅቷል። | በመቶኛ | 100 | 70 | 70 | |
| 1.2 | በሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም ግንባታ ጥናት መሠረት የአቅም ግንባታ ጉዳዮችን መለየት | • በቀጣይ በሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም ዝግጁነት የዳሰሳ ጥናት መሰረት የአቅም ግንባታ መርሃ-ግበር ይዘጋጃል። | በመቶኛ | 100 | 0 | 0 | የክትትልና ግምገማ አቅም ዝግጁነት የዳሰሳ ጥናት በረቂቅ ደረጃ ስለሚገኝ |
| 2 | የዲጅታል ክትትልና ሪፖርት ሥርዓትን (Digital Monitoring and Reporting Systeme software) ለመተግበር የለማውን ሶፍትዌር አሰራሩን በቅርብ መከታተልና የበለጠ እንዲሻሻል ማድረግ | • ለ26 መስሪያ ቤቶች በሁለት ዙር ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን የልማት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን በዲጂታል ሪፖርት ማቅረቢያ ሥርዓቱ በኩል ማቅረብ ከሚጠበቅባቸው 26 ተቋማት ውስጥ 11 ተቋማት አቅርበዋል።<br>• ከነዚህም ውስጥ 7 ያህሉ ደግሞ በቀረበው መመዘኛ መስፈርት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| | | መሠረት አጠቃላይ የልማት ዕቅድ ትግበራቸውን መዝነዋል። | | | | | |
| 3 | ለኮሚሽኑና ለአስፈፃሚ ተቋሚት ባለሙያዎች በImpact evaluation methods ላይ ስልጠና መስጠት | • ለመ/ቤቱ እና ለዘርፉ አስፈፃሚ ተቋማት ሰራተኞች የክትትልና ግምገማ አቅማቸውን ለማጎልበት በ Impact evaluation methods ላይ ስልጠና ተሰጥቷል። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 4 | ለተመረጡ ድርጅቶች የInvestment analysis/management ስልጠናዎችን መስጠት | • የስልጠና ሰነድ ተዘጋጅቷል። | በቁጥር | 1 | 0.75 | 75 | ከመጀመሪያው ስልጠና ጋር በነበረው የጊዜ መጣበብ ምክንያ ትስልጠና ሊሰጥ አልቻለም። |
| 5 | ለዘርፍ አስፈፃሚ መ/ቤቶች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | | | | | | |
| 5.1 | ከማህበራዊ ዘርፍ መ/ቤቶች ጋር ተናቦ በመስራት ቴክኒካዊ የምክር አገልግሎት በመስጠት ድጋፍ ማድረግ | • ለማህበራዊ ዘርፍ መ/ቤቶች የአፈፃፀም ሪፖርታቸውን እንዴት በተሟላ ሁኔታ ማዘጋጀት እንዳለባቸው ድጋፍና ክትትል ተደርጓል።<br>• የ100 ቀን እቅድን ጨምሮ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳዩ ሚኒስቴር ፣ በባህልና ስፖርት፣ በሰራተኛና ክህሎት እንደዚሁም በጤና ሚኒስቴር አጠቃላይ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ተደርጓል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 5.2 | ከመልካም አስተዳደርና ሰላም ዘርፍ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በክትትልና ግምገማ ላይ የምክር አገልግሎትና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | • በዘርፉ ካሉ ተቋማት የክትትልና ግምገማ ስራ ክፍል ሀላፊዎችና ባለሙያዎች በቀረቡ ጥያቄዎች እንዲሁም በሪፖርት አዘገጃጀት ላይ በታዩ ጉድለቶች ላይ ድጋፍ ተደርጓል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 6 | የፌዴራል ተቋማትን የፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ አሰራር፣ አደረጃጀትና የሰው ኃይል በዳሰሳ ጥናት መለየትና ድጋፍ ማድረግ | • ርዕስ የመለየት፣ የ2ኛ ደረጃ መረጃ የመሰብሰብ እና የአንደኛ ደረጃ መረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ የማዘጋጀት ሥራ ተከናውኗል።<br>• ነገር ግን የአንዳንድ የፌዴራል ተቋማት የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ የሥራ ክፍል ገና በመደራጀት ላይ በመሆኑ እና በጊዜ እጥረት ምክንያት መረጃው ተሰብስቦ የመተንተን ሥራ አልተከናወነም። | በቁጥር | 1 | 0.4 | 40 | ስራው 40 በመቶ የተከናወነ ሲሆን ቀሪው ሥራ በቀጣይ ሩብ ዓመት የሚከናወን ይሆናል። |

**ስትራቴጂክ ግብ 5፡- የልማት ዕቅድ ዝግጅት ከጥናትና ምርምር ጋር ያለውን ትስስር ማሳደግ (ክብደት 8)**

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 1 | የድህነትና የኑሮ ደህንነት ትንተና ሥራ ማካሄድ | | | | | | |
| 1.1 | በsurvey data management, በUni-dimentional and multi-dimentional የድህነት ትንተና ዘዴዎች ዙሪያ ሥልጠና መስጠት፤ | • በዚህ የጥናት መስክ ላይ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ | በመቶኛ | 50 | 50 | 100 | |
| 1.2 | ሀገራዊ የፊርጀ ብዙ የድህነት አመልካች/Multidimension Poverty Index/ የድህነት ትንተና ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት | • ከተለያዩ የድህነት አመልካቾች መካከል አንዱ የሆነውን የዘርፈ ብዙ የድህነት አመልካች (MPI) ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል የመነሻ የጥናት ሰነድ በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡<br>• የዘርፈ ብዙ ድህነትን ለመለካትና ለመተንተን የቤተሰብ ገቢና ወጪ የናሙና ጥናት (HCES) እና የኑሮ ደህንነት የናሙና ጥናት (WMS) መረጃዎች በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ፡፡<br>• የቅድመ ትንተና ሪፖርት ዝግጅቱ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን ጋር በጋራ ለመስራት ከስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ | በመቶኛ | 40 | 40 | 100 | |
| 1.3 | በድህነትና በኢ-እኩልነት መሀከል ያላቸውን መስተጋብር የሚያሳይ ጥናት ማካሄድ | • ኢ-እኩልነት በረዥም ጊዜ ሁኔታ ለድህነት መባባስ ምክንያት ሊሆን የሚችልባቸውንና የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖ ጥናት ለማጥናት የጥናቱ መነሻ ሀሳብ ተዘጋጅቷል፡፡<br>• በተጨማሪም ከ/WRI/ ጋር በመተባበር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ | በመቶኛ | 50 | 25 | 50 | |
| 2 | በኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ በ2014 ዓ.ም ጥናት ሊካሄድባቸው የሚገባ የጥናት መስኮችን በመለየት ጥናቶችን ማካሔድ | • አንድ የኢኮኖሚ ዘርፎች የዳሰሳ ጥናት ሀሳብ (መስክ) የማመንጨት፣<br>• ዝክረ ሃሳብ (Proposal) በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት የማቅረብ፣<br>• ጥናቱን በተቀናጀ መልኩ ለማካሄድ ይቻል ዘንድ በጥናቱ ላይ የሚሳተፉ አካላትን የመለየት እና<br>• ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን የማሟላት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ | በቁጥር | 1 | - | 25 | ስራው 25 በመቶ ተከናውኗል፡፡ በቀጣይ በዕቅዱ መሰረት የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ |
| 3 | የኢኮኖሚ ዘርፎችን የሚመለከት አለማቀፋዊ ፣አህጉራዊ፣ የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ክስተቶችን እና በዘርፍ ላይ ያሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ማሰባሰብና ትርጉም ባለው መልኩ | • ወቅታዊ የሆኑትን ዓለም አቀፍ ሁነቶች በመከታተል፣ በማሰባሰብና በማደረጃት<br>• የዘርፉን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በማደራጀት መረጃዎችን | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| | ማደራጀት | በተገቢው ሁኔታ ተንትኖ ለዘርፉ ክትትልና ግምገማ በግብዓትነት የማዋል ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ | | | | | |
| 4 | የማህበራዊ ዘርፎች (የጤና፣ ትምህርት እና የማሕበራዊ ጉዳይ እና የሴቶች ህፃናት እና ወጣቶች) ተያያዥ ዓለም አቀፍ የልማት አጀንዳ መረጃዎችን (time series data) ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ ማዘጋጀትና መጠቀም | • የማህበራዊ ዘርፎች (የጤና፣ ትምህርት እና የማሕበራዊ ጉዳይ እና የሴቶች ህፃናት እና ወጣቶች) ተያያዥ ዓለም አቀፍ የልማት አጀንዳ መረጃዎችን (time series data) ተዘጋጅቷል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 5 | ከዩኒሴፍ ጋር በመተባበር የአገራዊ የግምገማ አቅም ዳሰሳ ጥናት ማስተባበር | • የአገራዊ የግምገማ አቅም ዳሰሳ ጥናት የመጨረሻ ረቂቅ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 95 | 95 | |
| 6 | የብሔራዊ የሰው ሀብት ልማትና የስራ ገበያ ግምገማዊ ጥናት (National human capital development and labour market evaluation study) ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጥናት ማድረግ | • የብሔራዊ የሰው ሀብት ልማትና የስራ ገበያ ግምገማዊ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል ዝክረ ሃሳብ ተዘጋጅቷል፡፡ | በመቶኛ | 50 | 40 | 80 | |
| | **ስትራቴጂክ ግብ 6፡- ፖሊሲዎችና የልማት ዕቅዶች በመረጃና በትንታኔ ላይ የተመረኮዙ እንዲሆኑ ማድረግ፤ (ክብደት 8)** | | | | | | |
| 1 | ወቅታዊና ሁሉን አቃፊ የሆኑ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ሞዴሎችን መቅረጽ | | | | | | |
| 1.1 | ሀገራዊ የሶሻል አካውንቲንግ ሜትሪክስን ዝግጅት ማጠናቀቅ | • ሀገራዊ የሶሻል አካውንተንግ ሜትሪክስ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ውስጥ ተጠናቅቆ ሞዴሉን የማጸደቅ /Validate/ ስራ ብቻ ይቀረዋል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 95 | 95 | |
| 1.2 | ሲስተምስ ዳይናሚክስሞዴል (Systems Dynamics Model) ዝግጅት ማጠናቀቅ | • ባለፉት የበጀት ዓመታት ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ በሂደት ላይ ያለውን የሲስተምስ ዳይናሚክስ ሞዴል በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ውስጥ ተጠናቅቆ ሞዴሉን የማጸደቅ /Validate/ ስራ ብቻ ይቀረዋል፡፡ | በመቶኛ | 100 | 95 | 95 | |
| 1.3 | የማክሮ ኢኮኖሜትሪክ ሞዴል ማዘጋጀት | • በማክሮ-ኢኮኖሜትሪክስ ሞዴል ትግበራ ዙሪያ ለተቋሙ ሰራተኞችና ለሚመለከታቸው የአስፈጻሚ ተቋማት ወርክሾፖች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል፡፡ | በመቶኛ | 70 | 90 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| **ስትራቴጂክ ግብ 7: - የመንግስት ኢንቨስትመንት (ፕሮጀክቶች) አስተዳደር እና አመራር ውጤታማነትን ማሻሻል፤ (ክብደት 10)** | | | | | | | |
| 1 | የፌደራል መንግስት የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ እና የአዋጭነት ግምገማ (Project Prescreening and Appraisal) ማከናወን | • በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ እንዲሁም አዋጭነት ግምገማ ተዘጋጅቶላቸው ለቀረቡ የልማት ፕሮጀክቶች ግምገማ በማድረግ ውሳኔ እና ምላሽ ተሰጥቷል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | ይህ ተግባር በአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች በሚቀርብ ፕሮጀክት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ነው። በአስፈፃሚ መ/ቤቶች ተዘጋጅተው ለቀረቡ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ፕሮጀክቶች በቅደም ተከተል በአንድ፣ በሁለት እና በሶስት ወር ውስጥ ምላሽ ከተሰጠ ተግባሩ 100 በመቶ እንደተከናወነ ይቆጠሯል። |
| 1.1 | የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ማንዋሎች እና ቅፆችን ማሻሻል | • የፕሮጀክት ፅነሰ ሀሳብ፣ የአዋጭነት ጥናት እና የትግበራ ዕቅድ መመሪያዎች ያለባቸውን ክፍተት ለመሙላት መመሪያዎቹ እንዲሻሻሉ ተደርጓል። | በቁጥር | 2 | 3 | 100 | ስራው በአለም የገንዘብ ድርጀት በተደረገ ድጋፍ መሰረት ተከናውኗል። |
| 1.2 | በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ በማከናወን ምክረ ሀሳብ ማቅረብ | • በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ቀረቡ ፕሮጀክቶች መጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ተከናውኖባቸው ለምላሽ ዝግጁ ሆነዋል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 1.3 | የአዋጭነት ጥናት ተዘጋጅቶ የቀረበባቸውን ፕሮጀክቶች በመገምገም ምክረ ሀሳብ ማቅረብ | • ከግብርና እና መስኖ፣ ከከተማ ልማት፣ ከከፍተኛ ትምህርት ሴክተሮች እና ከተለያዩ የፌደራል መ/ቤቶች የቀረቡ የፕሮጀክቶች አዋጭነት ጥናት ላይ የአዋጭነት ግምገማ በማከናወን ለምላሽ ዝግጁ ሆነዋል።<br>• ከተለያዩ የፌደራል አስፈፃሚ መ/ቤቶች በአዋጁ መሰረት ወደ ቀጣይ ሂደት አልፈው የአዋጭነት ግምገማ የቀረበባቸው ፕሮጀክቶች አስፈፃሚ መ/ቤቶች የአዋጭነት ጥናት እንዲያጠኑ አስፈላጊ ድጋፍ ተሰጥቷል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | የግልገል አባይ፤ ቦረና፤ የገላና እና የሸንሌ የመስኖ ፕሮጀክቶች ዘግይተው የቀረቡ ፕሮጀክቶች በመሆናቸው አሁኑ ወቅት ግምገማ እየተደረገባቸው ነው። |
| 1.4 | በፕሮጀክቶች አዋጭነት ጥናት ዝግጅት እና የቅድመ ትግበራ ግምገማ ላይ የአሰልጣኖች ስልጠና መስጠት | • ለመ/ቤቱ የፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማ ባለሞያዎች የቴክኒካል ስልጠና ለመስጠት ዝግጅት ተጠናቋል፤<br>• ለአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ባለሞያዎች የፕሮጀክት ዝግጅት ስልጠና ለመስጠት ዝግጅት ተደርጎ፤<br>• ከአለም ባንክ እና ከኪዊንስ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር የአንድ ወር የአሰልጣኞች ስልጠና ለሰባት ባለሞያዎች ተሰጥቷል። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 1.5 | በፌደራል መንግስት የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ስርዓት እና በፕሮጀክቶች የፅንሰ ሀሳብ እና የአዋጭነት ጥናት እና ግምገማ ላይ የግንዛቤ መስጫ መድረኮች ማከናወን | • የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በታቀደው መሰረት የተዘጋጀ ባይሆንም በተለያዩ መድረኮች ግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል። | በቁጥር | 2 | - | - | የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በሌሎች መድረኮች የተሰጠ ሲሆን የታቀደው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በቀጣይ ከቴክኒካል ስልጠና ጋር በማስተሳሰር የሚከናወን ይሆናል |
| 2 | የተሻሻለ የፕሮጀክቶች የኢኮኖሚ መለወጫ እና መመዘኛ መመሪያ (Standard Economic Converstion Factor and Parameter) | • የተሻሻለ የፕሮጀክቶች የኢኮኖሚ መለወጫ እና መመዘኛ መመሪያን ለመከለስ የሚስችል የስራ መዘርዝር ተዘጋጅቷል።<br>• የኬኒያን እና ኡጋንዳን ተሞክሮ በአለም የገንዘብ ድርጅት አማካኝነት ለመዳሰስ ተሞክሯል።<br>• መመዘኛ መስፈርቱን ወቅታዊ ለማድረግ የስራ መዘርዝሩን በድጋሚ የመፈተሽ እንዲሁም ተሞክሮ የመቀመር ስራ ተሰርቷል። | በቁጥር | 1 | - | - | በቀጣይ በዕቅዱ መሰረት የሚጠናቀቅ ይሆናል። |
| 3 | የ10 ዓመት የልማት ዕቅድን ለማስፈፀም የመንግስት የኢንቨስትመንት ፕላን ማዘጋጀት (Public Investment Resource Envelope Plan) | • የሴክተሮችን የኢንቨስተመንት የትኩረት አቅጣጫ የሚያሳይ የኢንቨስተመንት ፕሮግራም በማዘጋጀት ለሴክተሮች ተደራሽ በማድረግ በልማት ፕሮግራም እንዲያዝ ተደርጓል።<br>• የከፍተኛ ትምህርት የመንግስት ኢንቨስትመንት አስተዳደር የሚመራ አመላካች ረቂቅ ስትራቴጂ ተቀርፃል። | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | ረቂቅ የመንግስት ኢንቨስትመንት ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለዘርፎች ቀርበዋል።<br>በቀጣይ ፕሮግራሞችን መሰረት ያደረገ ፕሮጀክት እንዲቀርብ ክትትል ይደረጋል። |
| 4 | በተመረጡ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮች ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ማንዋል ማዘጋጀት | • ለተመረጡ ሴክተሮች የፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት ማንዋል ለማዘጋጀት መረጃ የማሰባሰብ እና ተሞክሮ የመቀመር ስራ ተሰርቷል። | በቁጥር | 3 | - | 66 | ስራው 66 በመቶ ተከናውኗል።<br>በቀጣይ ዝርዝር ሴክተር ማንዋሎች ይዘጋጃሉ። |
| 5 | ለፕሮጀክቶች የአዋጭነት ዝግጅት ግብዓት የሚያገለግል የፕሮጀክት የግብዓት እና የዋጋ መረጃ ቋት ማዘጋጀት | • ቀደም ብለው የቀረቡ እና የተገመገሙ ፕሮጀክቶች መረጃ የማደረጃት ስራ ተሰርቷል። | በመቶኛ | 50 | 50 | 100 | በቀጣይ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች በዚህ የመረጃ ቋት ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል። |
| 6 | በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች የመንግስት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ስርዓት ላይ ስልጠና ማከናወን | • ለሀረሪ ክልል፣ ለሶማሌ እና ለሲዳማ ክልል ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ስልጠና ተሰጥቷል። | በቁጥር | 2 | 2 | 100 | ከታቀደው ውጭ በሌሎች አማራጮች የታቀዱ ስልጠናዎች ለክልሎች እንዲሰጡ ድጋፍ ይደረጋል |
| | **ስትራቴጂክ ግብ 8: - ብሔራዊ ኢኮኖሚ አመላካች መረጃዎችን ማመንጨትን ማጎልበት፤ (ክብደት 10)** | | | | | | |
| 1 | እየተሰሩ ያሉትን የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንቶችን ማዘጋጀት እና ስርጭትን ማሻሻል | | | | | | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| 1.1 | የ2013 በጀት ዓመት የሀገር ውስጥ ምርት ከአቅርቦት አንጻር (Supply side GDP) እና ከአጠቃቀም አንፃር (Expenditure Side) GDP) ትመና አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብና በማጠናቀር (በመገመት) ለተጠቃሚዎች ማቅረብ | • የ2013 በጀት አመት በጊዜውና በቋሚ አመት ዋጋ የተሰላ አመታዊ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት Supply Side GDP እና ከአጠቃቀም አንፃር (Expenditure Side GDP) ግመታ ተዘጋጅቶ ቀርቧል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 1.2 | የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት አመታዊ ሪፖርት ከሚይዘዉ መረጃ በተጨማሪ የትንተና ሪፖርት Analytical report) ማዘጋጀት። | • አመታዊ የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ቀርቧል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 1.3 | የዓመታዊ ሀገራዊ ምርት ግመታ ከአቅርቦት አንጻር Supply side GDP) እና ከአጠቃቀም አንፃር (Expenditure Side) ጊዜያቸውን ጠብቀው የተከለሱ መረጃዎች ለመንግስትና እንዲሁም መንግስታዊ ላልሆኑ ተጠቃሚዎች ማሰራጨት | • የዓመታዊ ሀገራዊ ምርት ግመታ ከአቅርቦት አንጻር (Supply side GDP) እና ከአጠቃቀም አንፃር (Expenditure Side) ጊዜያቸውን ጠብቀው የተከለሱ መረጃዎች ለመንግስትና እንዲሁም መንግስታዊ ላልሆኑ ተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል። | በመቶኛ | 100 | 80 | 80 | |
| 2 | ተጨማሪ የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንቶችን ማዘጋጀት | | | | | | |
| 2.1 | የ2013 4ኛው ሩብ ዓመት እና የ2014 ሩብ ዓመታዊ የሀገር ውስጥ ምርት ግመታ ከአቅርቦት አንጻር (QGDP - Supply side) ማዘጋጀት | • የ2013 4ኛው ሩብ ዓመት የሀገራዊ ምርት ግመታ (QGDP - Supply side) ከአቅርቦት አንጻር ተዘጋጅቷል።<br>• የ2014 1ኛው ሩብ ዓመት የሀገራዊ ምርት ግመታ (QGDP - Supply side) ከአቅርቦት አንጻር ተዘጋጅቷል። | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 2.2 | የሀገር ውስጥ የሩብ አመት ምርት ግመታ ከአቅርቦት አንጻር (QGDP - Supply side) የመረጃ ሽፋን፣ ጥራት፣ ወቅታዊነት እና አስተማማኝ ሆነዉ በተገኙ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ የአገማመት ዘዴ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ Gap Assessment እና መረጃዎችን ማሰባሰብ | • በግብርና ሴክተር ዙሪያ ያሉ አመላካቾች (Activity calendar ratios) ላይ ከግብርና ሚኒስቴር እና ከሌሎች የጥናት ተቋማት ጋር ውይይት ተደርጓል። | በመቶኛ | 100 | 5 | 5 | ስራው 5 በመቶ ተከናውኗል። በቀጣይ በዕቅዱ መሰረት የሚከናወን ይሆናል። |
| 3 | የክልል ኢኮኖሚ አካውንት አዘገጃጀት ሥርዓት መዘርጋት እና የአቅም ግንባታ ሥራዎች መሥራት | | | | | | |
| 3.1 | የብሔራዊ/ክልላዊ ኢኮኖሚ አካውንት አዘገጃጀት መሠረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች እና ሥልጠና መስጠት | • የብሔራዊ/ክልላዊ ኢኮኖሚ አካውንት አዘገጃጀት መሠረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች፣ በመረጃ ሽፋን እና ምንጭ፣ በአሰራር ዙሪያ ለአዲሱ ሲዳማ ክልል ስልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም ለኦሮሚያ ክልል የቴክኒክ | በቁጥር | 3 | 2.25 | 75 | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | |
| | | ድጋፍ ተደርጎዋል። | | | | | |
| 3.2 | የክልል ኢኮኖሚ አካውንት በተመለከተ ድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ክልላዊ ግምት የማዘጋጀትና የማከፋፈል (Allocation of trans regional /cross border economic activities) ሥራዎችን ላይ ከባለድረሻ አካላት ጋራ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ | • በገቢ ግብር ታክስ መረጃ በክልል ደረጃ ማጠቃለል እንዲቻል እንዲሁም በየኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን መረጃዎች ማግኘት በሚቻልበት ዙሪያ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋራ ውይይት ተደርጎ መግባባት ላይ ተደርሷል።<br>• ከገቢዎች ሚኒስቴር የአምስት አመት መረጃዎች በመጠበቅ ላይ ይገኛል። | በቁጥር | 2 | 1 | 50 | |
| 3.3 | የክልል ኢኮኖሚ አካውንት መረጃዎች ከብሔራዊ አካውንት አሠራር ስርዓት ጋር በተጣጣመና ደረጃውን የጠበቀ የክልል አካውንትን አሰራር ስርዓት በተቀናጀ መልኩ ለማስኬድ ይቻል ዘንድ ከክልሎች ጋር ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ማጎልበት፣ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠትና ማስተባበር | • ለአዲስ አበባና ለኦሮሚያ ክልል የቴክኒክ ድጋፍ በኢሜል፣ በስልክ እና በአካል ተሰጥቷል። በተጨማሪም የመረጃ አቅርቦት ስራ ተሰርቷል። | በቁጥር | 4 | 2.6 | 65 | በቀጣይ መዕቅዱ መሰረት የሚጠናቀቅ ይሆናል። |
| 3.4 | የተጣጣመ እና ደረጃውን የጠበቀ የክልል ኢኮኖሚ አካውንት አሠራር መመሪያ ማጠናቀቅ | • ከውጭ አማካሪ ጋር በርካታ ስራዎችን በማከናወን የኢትዮጵያ የክልል ኢኮኖሚ አካንት መመሪያ (Sources and methods manual) ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።<br>• በየኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በብሔራዊ እና በክልል ደረጃ ምን እንደሚመስል የNarrative ስራ ፣ ለክልሎች የተዘጋጀው Excel Template ወደ ወርድ መቀየር (How to read the template) እና በተለይ አብዛኞቹ የአገልግሎት ዘርፍ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ወደ ተሻለው የታክስ መረጃ መስራት ማስላት እንዲቻል ቴምፕሌቶች የመቀየር ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል። | በመቶኛ | 100 | 90 | 90 | |
| **ስትራቴጂክ ግብ 9፡- የስነ ህዝብ ባህሪያትን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር እንዲጣጣም ማገዝ፤ (ክብደት 10)** | | | | | | | |
| 1 | ለሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ክለሳ፣ ለልማት ዕቅዶች ግብአት የሚሆኑ ጥናቶችን እና የሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ክለሳ ማካሄድ | | | | | | |

| ተ.ቁ | በ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ | መለኪያ | የ2014 በ.ዓ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | | ምርመራ |
